# አውራ አልባ ንቦች

***ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ***

**አውራቸውን አቅፈው ጠላት እንዳይገባ፥**
**ቀፎውን ጠብቀው ሳይዘረፍ ማሩ፥**
**ንቦቹ ተባብረው ተረባርበው በፍቅር፥**
**ሲያስቀኑ፥ ሲሉ ደስ፥ ሁሉም እያማሩ፥**
**ዝንቦች ተቃጠሉ ብው አሉ በቅናት፥**
**ንቦችን ለማጥፋት ታላቅ ሤራ አሤሩ፤**
**ማሩንም ሊበሉ መላዎች ፈጠሩ፤**
**ተመካከሩናም ታላቅ ተንኮል ሠሩ፡፡-**

**“አውራ አያሻችሁም፥” አሏቸው ንቦቹን፥**
**“አውራውን ተዉና ሂዱ በየፊና**
**“ባውራው ፈንታ እናንተ እንድትሆኑ አውራ፥**
**“የአውራውን ሥልጣን ንጠቁት ባፈና!**
**“ይህን ብታረጉ ነጻነት ወጥታችሁ**
**“ትፈነጫላችሁ እንደፈቀዳችሁ**
**“ስለዚህ ተነሱ! አምጹ ባውራው ላይ**
**“አመጹን በወጉ እየአቀዳችሁ!”**

**ይህንን ሲሰሙ ፈነጠዙ ንቦች**
**ታያቸው ሲሆኑ ሁላቸውም አውራ**
**ባውራቸው አሲረው ሁር ወጥተው በሜዳ**
**ወዲያ ወዲህ ሲሉ ትተው የማር ሥራ፡፡**

**በዝንቦቹ ተንኮል ተመርተው ንቦቹ**
**ባውራቸው አምጸው፥ አውራቸውን ከድተው፥**
**ቀፎአቸውን ለቀው፥ በያቅጣጫው ከንፈው**
**ፈነጩ፥ ፎለሉ ባገሩ፥ በፍንጥዝ ፈንድተው፡፡**

**ዝንቦቹ እየሳቁ፥ ገብተው እቀፎው ውሥጥ፥ማሩን**
**እየዋጡ፥ አውራውን ለብቻው አግኝተው በግላጭ፥**
**“ደሞ አንተ ብሎ አውራ! ተመልከት ንቦችህ ያንተን**
**“ሥልጣን ነጥቀው የትም ሲፎልሉ፥ አንተ ሆነህ ቀላጭ!**

“በታትነናችሁአል በመሰሪ ተንኮል” እያሉ አላገጡ
“እናንተን አውድመን ልንሆን ቀራጭ ፈላጭ!”

ንቦቹ አውራ ሆነው ነግሠው በየፌና
እዛም እዚህ ሲሉ ቆዩና ፈንጭተው
ሥራቸውን ትተው ሆነው ሥርዓተ-አልባ፥
አለቁ በዝንቦች አንድ ባንድ ተፈጭተው።

ላዳማጭ አስደንጋጭ፥ ለሰሚው ነው ግራ፥
አይመችም ለሰው ይህንን ቢል ላውራ-
ንብ አውራውን ትቶ፥ ማር መሥራት ዘንግቶ፥ወደ
አሻው በርሮ፥ እኔ ነኝ ሲል መሪ፥ እኔ ነኝ ሲል አውራ!

እኤአ መሥከረም 20 ቀን 2007